የሰ/መ/ቁ. 42714

ኀዳር 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትሕና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ - ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ገ/ማርያም ዋዴሮ ቀረበ

2. አመሃ ጥበቡ ቀረበ

3. በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት - ሽምሱ ስሩር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከቤት ባለቤትነት መብት ጋር ተያይዞ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ አቅርቦ ከተከራከሩ በኂላ፣ ክስ ያቀረበበትን ቤት እንዲረከብ ውሣኔ አሰጥቶአል፡፡ አመልካች መቃወሚያ ያቀረበው ቤቱ ከጅምሩ የአስተዳደሩ ሲሆን ዋጋ ተቀብሎ ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈው በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ይነካል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን ከመረመረ በኂላ፣ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች መብቴ ተነክቶአል በማለት ያቀረበው የመቃወሚያ ክርክሩ ሣይሰማ ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ባቀረበው መቃወሚያ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ በመሆን ሊያቀርበው ይችል የነበረውን የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር እንዲያሰማ አልተደረገም፡፡ በሰበር አቤቱታው እንደገለፀው በጉዳዩ ያገባኛል የሚለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 2/95 እና በአዋጅ ቁ. 4/2000 /እንደተሻሻለ በአንቀጽ 29 መሠረት የተቋቋመ የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካል በመሆኑ ነው፡፡ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 29/3/ መሠረት የከተማውን አስተዳደርና የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር መብት የተሰጠው መሆኑንም በክርክሩ ገልጾአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 በተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ለክርክሩ መሠረት ከሆነው ቤት ጋር በተያያዘ ያለውን የከተማውን አስተዳደር የነዋሪዎች መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚል እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

አስቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ ለማስነሣት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ ውስጥ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ፤ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድም መብቱን የሚነካበት የሆነ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች በአስተዳደሩ የአስፈፃሚ አካልነቱ ሊያስጠብቀው የሚገባው የአስተዳደሩና የነዋሪዎች መብትና ጥቅም እንዳለ በመግለጽ መቃወሚያውን አቅርቦአል፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት ፍ/ቤት ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ በተደነገገው መሠረት ክርክሩን አልሰማም፡፡ አቤቱታውን ውድቅ ያደረገው ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ መብቱ ከተነካ "በሕግ አግባብ ውሣኔውን ከሚያስለውጥ በቀር ... በዚህ ረገድ ሊያቀርበው የሚችለው የመቃወም አቤቱታ ... የለም" የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ ይህን አይነቱ አካሄድ አግባብ ያለውን የሥነ ሥርዓቱን ድንጋጌ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ አመልካች ቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቴ ተነክቶአል ማለቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማስለወጥ የሚችለው መቃወሚያውን በማቅረብ ነው በፍ/ቤቱ ግንዛቤ ሣያገኝ ቀርቶአል የምንለውም ይህ ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሥነ - ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 71179 ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 75281 ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ በጉዳዩ ሥረ ነገር ግራ ቀኝ ወገኖችን አከራክሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ